በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር 04/30/7/9006
Ref.No
ቀን 3/11/2015
Date

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- <u>የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል፤</u>

በአገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የተሽከርካሪዎች ቁጥር በፖሊሲ ማዕቀፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የሚስማማ፣ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል፣ በአየር ንብረትና በብዝሃ ህይወት ላይ ተጽእኖ የማያሳርፍ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በአግባቡ የሚጠቀም የመጓጓዣ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን እና አስመጪዎች የሚያበረታታ የታክስ ፖሊሲ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የቤት አውቶሞቢሎች እና የእቃ መጫኛ ተሽከርካሪዎች ላይ ዝቅተኛ የጉምሩክ ታሪፍ የተጣልባቸው እና ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ነፃ ቢደረጉ በአገር ውስጥ የሚመረቱትም ሆነ ከውጭ የሚገቡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው እንዲቀርቡ ያስችላል።

ስለዚህ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 129 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 8(4) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ሊፈቅድ እንደሚችል በተደነገገው መሠረት፡-

1. ታሪፍ ቁጥር 8702.4010 ላይ የሚመደቡ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

Hima _ Tax Solutions
CamScanner

Hima _ Tax Solutions

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር _____
Ref.No
ቀን _____
Date

2. ታሪፍ ቁጥር 8703.8011፣ 8703.8012 እና 8703.8013 ላይ የሚመደቡ ተሸከርካሪዎች የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ እንደሚከተለው እንዲሆን፣

ታሪፍ ቁጥር	ጉምሩክ ቀረጥ	ኤክሳይዝ ታክስ	ተጨማሪ እሴት ታክስ	ሪ ታክስ
8703.8011	0%	0%	0%	0%
8703.8012	5%	0%	0%	0%
8703.8013	15%	0%	0%	0%

3. ታሪፍ ቁጥር 8704.6011 ላይ የሚመደቡ በአገር ውስጥ እንዲገጣጠሙ መሉ በሙሉ የተበታተኑ (CKD) ተሽከርካሪዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

4. ታሪፍ ቁጥር 8703.6012 ላይ የሚመደቡ በአገር ውስጥ እንዲገጣጠሙ በከፊል የተበታተኑ (SKD) ተሽከርካሪዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

5. ታሪፍ ቁጥር 8703.6013 ላይ የሚመደቡ ሙሉ በሙሉ የተገጣጠሙ (CBU) ተሽከርካሪዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ፤

የተወሰነ መሆኑን እየገለጽን፤ ማሻሻያው ይህ ደብዳቤ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ኢሶግ ተክለኃ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ገንዘብ ሚኒስቴር
ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ስልክ 251-11-155 24 00, 22 66 98
የፖ.ሣ.ቁ P.O.BOX 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
MoF_Ethiopi
facebook.com/MoFEDet

CamScanner